# መቾ ዋዛ!




የከረምቦላ ቤት ጉዶች መከማቻ፣
የቢራ መጠጫ፣ ካርታ መጫወቻ፣
መቀለጃ ሆንኩኝ በሓሜት ሽኩቻ፣
ይዘው ቸበቸቡኝ በውሸት ዘመቻ፣
ነከሱኝ፣ አኘኩኝ በወሬ ፍትፍቻ።

ደካማ ነው ብለው ቢያዩኝ ብቻዬን
ሞከሩ ለመፍታት መቀነቻዬን።



በሆነ ባልሆነ አሙኝ፣ ፈተፈቱኝ፣
ብለው ሊያሳስቱኝ፣ እጅግም ሊያምታቱኝ፣
ቀበቶየን ይዘው፣ ሳቡና ጐተቱኝ…
መች ዋዛ ሆነ'ና የኔ መቀነቻ፣
በከንቱ አይፈታም በወሬ ፍትፍቻ!

ከንፈሬን ነክሼ፣ ውጫለሁ ምራቂ፣
ዋዛ መስያቻው… ብቀጥንም አረቄ!

ገ/ኢ. ጐርፉ።